# የሃይማኖት ሬዲዮና ቴሌቪዥን ፈቃድ አሰጣጥ ረቂቅ መመሪያ ላይ የተሰጠ የባላሞያዎች አስተያየት

### (በሕግ ባለሞያዎች አብይ ኮሚቴ የሰነድ ዝግጅትና ረቂቅ ን/ኮሚቴ)

(1) በሚዲያ አዋጁ መሰረት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ደንብ፤ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ደግሞ በግልጽ በተቀመጠለት ጉዳዮች ላይ ብቻ መመሪያ ለማውጣት ስልጣን እንደተሰጠው ይገልጻል (አንቀጽ 90(1) & (2))። ነገርግን የሃይማኖት ብሮድካስትን በተመለከተ አዋጁ በግልጽ መመሪያ የማውጣት ስልጣን ያልሰጠ በመሆኑ፤ እንዲሁም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ገና ደንብ ያላወጣ በመሆኑ ይህንን መመሪያ ለማውጣት ባለስልጣኑ የሕግ ድጋፍ ስለመኖሩ የተገለጸ ነገር የለም። ስለዚህ ይህ መመሪያ ከመውጣቱ አስቀድሞ የሕ/ተ/ምክር ቤት ደንብ ሊያወጣና የሃይማኖት ጉዳዮችን በተመለከተ በግልጽ መመሪያ እንዲወጣለት ማመልከት ይገባዋል።

(2) መምሪያ መሰረታዊ የሃይማኖት ብሮድካስት ባህሪያትን እንደ መደበኛው የብሮድካስት አገልግሎት የወሰደው ይመስላል። መጀመሪያ በግልጽ መቀመጥ ያለበት (በጥናት ሊሆን ይችላል)፤ አሁን ያለው የሃይማኖት ብሮድካስት ምን ችግሮች አሉበት፤ በተለይ ከይዘት አንጻር፤ የሃይማኖት ነጻነትን ከማክበር፤ የመንግስት እና ሃይማኖት መለያየት አንጻር፤ ከትውልድ ግንባታ፤ ከሰላምና ደኅንነት፤ በሃይማኖት ተቋማት እና በሚዲያ ባለቤቶች መካከል ያለው መስተጋብር ወዘተ። ይህ ከተለየ በኋላ የተለዩትን ችግሮች በሚፈታ መንገድ ትኩረት ተሰጥቶ የፍቃድና ምዝገባ ሥርዓት ሊዘጋጅ ይችላል። አሁን የተዘጋጀው መመሪያ በአብዛኛው የመደበኛ ብሮድካስት አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን የሚመለከቱ ነገርግን ለሃይማኖት ብሮድካስት ብዙም ጥቅም የሌላቸውን አንቀጾች በዝርዝር አስቀምጦ፤ በተቃራኒው ከላይ የተዘረዘሩትን ጥቂቱን በግርድፉ መጨረሻ ላይ አስቀምጦታል። እንደ የሃይማኖት ነጻነትን ማክበር፤ የመንግስት እና ሃይማኖት መለያየት፤ ትውልድ ግንባታ፤ ሰላምና ደኅንነት ወዘተ አንጻር የፕሮግራም ይዘት ወይም ግዴታ በተቋማቱ ላይ ሊጥል ይገባዋል። ስለሆነም የመመሪያው አንቀጽ 16 በበለጠ ተፍታቶ እንደ መሪ እሴት በመመሪያው የመጀመሪያ አንቀጾች ላይ መቀመጥ ይኖርበታል።

(3) የመመሪያው መሰረታዊ ድክመት በግለሰብ ደረጃ እራሱን ችሎ የሚቋቋም እና በሃይማኖት ተቋም ጥላ ሥር ሆኖ የሚንቀሳቀስን ሚዲያ በአንድ ዐይም ማየትና በተመሳሳይ መንገድ እንዲስተናገዱ መጠበቁ ነው። የሕግ እውቅና ያለው የሃይማኖት ተቋም ሲመሰረት ጀምሮ የሃይማኖቱን አስተምህሮ የሚያስተላልፍበት የተለያዩ ዘዴዎችን ለመጠቀም ተፈቅዶለት እውቅና የሚሰጠው በመሆኑና የሚዲያ ክፍሉም ከተቋሙ መዋቅር ጋር ተቀናጅቶ የሚሰራ በመሆኑ የበለጠ ሃላፊነትና ክትትል የሚደረግበት ነው።

- ለምሳሌ በሕግ የተቋቋመ የሃይማኖት ተቋም፤ ሕጋዊ ሰውነቱ የሚመነጨው ከሕግ ስለሆነ ወደ ሰላም ሚንስቴር በመሄድ የድጋፍ ደብዳቤ የሚጠይቅበት አግባብ ተጨማሪ ቢሮክራሲ መፍጠር ካልሆነ በቀር አላስፈላጊ ነው። ስለዚህ የአንቀጽ 5(ሐ) ተፈጻሚነት ወሰን በግልጽ መቀመጥ አለበት
- ፍቃዱን የሚሰጠው ብሮድካስት ባለስልጣን የሃይማኖት ድርጅቱ በሕግ የተቋቋመ አልያም በሕግ አግባብ የተመዘገበ መሆኑን ማወቅ በቂው ሆኖ ሳለ ከመዝጋቢው አካል ፍቃድ ወይም ድጋፍ የሚጠይቅበት አግባብ አላስፈላጊ እንግልት የሚፈጥር ካልሆነ በቀር ጥቅም የለውም
- አንቀጽ 7(3) የሃይማኖት ድርጅትን እንዲመዘግብ ስልጣን የተሰጠው ተቋም (ለምሳሌ ፍትሕ ሚንስቴር ወይም የሰላም ሚንስቴር) በማቋቋሚያ አዋጁ ወይም በሌላ ሕግ የሃይማኖት ብሮድካስት ለማቋቋም የሚፈልጉ ግለሰቦችን ወይም ተቋም ለመመዝገብ የሚያስችለው ሥርዓትና ሥነሥርዓት መኖሩን ማጣራት ያስፈልጋል።

(4) በረቂቁ ውስጥ የፍትሕ ሚንስቴር ወይም አሁን ባለው የአስፈጻሚዎች የሥራ ክፍፍል መሰረት የሃይማኖት ተቋማትን የመመዝገብ ስልጣን የተሰጠው የሰላም ሚንስቴር ከፍተኛ ሚና ተሰጥቶታል፡፡ እንዲያውም ባለሥልጣኑ ሙሉ ሥልጣኑን ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እጅ መንሻ አድርጎ የሰጠው አስመስሎታል፡፡ ነገር ግን ይህ በአዋጁ ውስጥ አይገኝም፡፡ የአስፈጻሚ አካላትን በሚያቋቁመው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 41(1)(ኀ) ውስጥ የሰላም ሚንስቴር የሃይማኖት ድርጅቶችንና ፍትህ ሚኒስቴር ደግሞ ማኅበራትን ከመመዝገብ ባለፈ የሃይማት ሚዲያ ሲቋቋም እንዲፈቅዱም ሆነ የድጋፍ ደብዳቤ እንዲጽፍ ወይም እድሳት ላይ አስተያየት እንዲሰጥ ስልጣን አልተሰጣቸውም:: ይህንን ስልጣን እንወጣው ቢሉም፤ ለዚህ የሚሆን የአሰራር ሥነሥርዓት ቀድሞ ካልተበጀ በቀር አላስፈላጊ እንግልትና ቢሮክራሲ መጨመር ነው። መሰረታዊው ጥያቄው ግን የፍትሕ ሚንስቴር/የሰላም ሚንስቴር አንድን የሃይማኖት ተቋም ከመዘገበ በኋላ ለሁለተና ጊዜ ፍቃድ አልያም የድጋፍ ደብዳቤ የሚሰጥበት አግባብ ለምን አስፈለገ፤ ይህንንስ በማድረግ የሚጨምረው እሴት ምንድነ ነው የሚለው ነው። በእኔ አስተያየት ምንም ነው።

(5) የታወቀ ወይም የተመዘገበ ሃይማኖት ሳይኖር የብሮድካስት አገልግሎት መስጠትም ሆነ ፍቃድ መጠየቅ በግልጽ መከልከል ይኖርበታል። የሚሰጠው ፍቃድም የታወቀው የሃይማኖት ተቋም የበላይ ሃላፊዎች በሚሰጡት የድጋፍ ወረቀት ወይም መጠይቅ ላይ ተመርኩዞ መሆን ይኖርበታል። ይህውም ሌላውን ሃይማኖት ለማጥላላት ወይም በሚዲያ ዘመቻ ሁከት በመፍጠር የተለየን ሃይማኖት ለማጥቃት ብቻ ተብሎ የሚቋቋምን ብሮድካስት አገልግሎት ማገድ ያስችላል። አሁን በተካተተው አንቀጾች መሰረት ግን "አመልካቹ የሃይማኖት ድርጅት ካልሆነ የሃይማኖት ድርጅቶችን እንዲመዘግብ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው የሚመለከተው አካል ወይም በሠላም ሚኒስቴር የሃይማኖት ብሮድካስት

እንዲያቋቁም የተፈቀደለት ወይም የተመዘገበ" (አንቀጽ 9(1)(ሀ)) ከሆነ ፍቃድ እንዲሰጠው ይፈቅዳል። ይህ የሃይማኖት ብሮድካስት የሚሰራጨው 'ለሃይማኖቱ ተከታዮች' መሆን አለበት ከሚለው ጽንሰ-ሃሳብ ጋር ፈጽሞ ተቃራኒ ነው።

(6) የአዋጁ አንቀጽ 31 መሰረት የፍቃድ አይነቶች የሕዝብ ብሮድካስት፤ ልዩ የሕዝብ፤ የንግድ እና የማኅበረሰብ ብሮዴካስት አገልግሎት ፍቃድ ብሎ የሚከፍላቸው ሲሆን አሁን የተረቀቀው መመሪያ ለሃይማኖት ተቋማት የሚሰጥ የብሮድካስት ፍቃድ ምን ሊሆን እንደሚችል አልደነገገም። ለሃይማኖት ተቋም የሚሰጠው የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አይነት በማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ስር ሊሸፈን ስለመቻሉ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውንም የአንዳንድ ሀገራት ልምድ መሰረት በማድረግ፤ በኢትዮጵያም ተመሳሳይ አሰራር ተግባራዊ ቢደረግ ጥሩ ይሆናል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ከተለያዩ የገቢ ምንጮች ወይም ከብሮድካስት አገልግሎቱ የሚገኘው ገቢ ለማሰራጫ ጣቢያው አገልግሎት ብቻ ወይም በተወሰነ መጠን ለሃይማኖቱ እንቅስቃሴ ብቻ እንዲውል ገደብ ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡

(7) በሃይማኖት ተቋማት ባለቤትነት የተያዘ የብሮድካስት ድርጅት ከመንግሥትና ከግል ዘርፉ፣ እንዲሁም ከሌሎች ተዋንያን ተጽዕኖ ነጻ ሊሆንም ይገባል፡፡ ይኸውም በመመሪያው ላይ በግልጽ መቀመጥ ሲኖርበት፤ ከተቋማት በልግስና ወይም በማስታወቂያ ያገኘውነ ገንዘብ በተለየ መንገድ ሪፖርት በማድረግ ይዘቱ ላይ ምንም ተጽኖ እንዳላመጣ እንዲያስረዳ ማድረግ ይገባል። ይኸንን ማድረጉ ለብሮድካስት ተቋሙም ለሕዝብ ደህንነትም ወሳኝ መሆኑን ማስታወስ እወዳለሁ። ስለሆነም የመመሪያው አንቀጽ 15(2) እንደአስገዳጅ ቅድመ ሁኔታ እንጂ እንደመብት ሆኖ መቀመጥ የለበትም።

(8) በመገናኛ ብዙኃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 አንቀጽ 70 ላይ እንደተደነገገው፣ ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ በሚያሰራጨው ሃይማኖት ተኮር ፕሮግራም ለሁሉም ሃይማኖቶችና እምነቶች ተገቢ ክብር እንደተሰጣቸው ማረጋገጥ አለበት፡፡ የሃይማኖትና የእምነት ነፃነትንና መሰረታዊ ሰብአዊ መብትን ሊጠብቅም ይገባል፡፡ አሁን የረቀቀው መመሪያ እነዚህን ግዴታዎች ያካተተና ተጠያቂነትንም በዚሁ አግባብ የሚያረጋግጥ ሊሆን ይገባል፡፡

(9) ከይዘት ክትትል ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው ጉዳይ ማስታወቂያ ሲሆን፣ በሌሎች ሕጎች ያልተከለከለ ይዘት ያለው ማስታወቂያ መሆኑን፣ ታማኝ የሆነ፣ ተመልካቹን የማይጎዳ፣ የማያሳስት እና ተገቢ በሆነው የአየር ሰዓት ማስተላለፍ ዋነኞቹ ናቸው፡፡ ሃይማኖትን የተመለከቱ ማስታወቂያዎችም የፕሮግራሙን ተከታዮች የማያሳስቱ፣ በሌሎች ሃይማኖቶች ላይ የጥላቻ ይዘት ያለው መልዕክት የማያቀርቡ፣ የሚተዋወቀው ሃይማኖት ተከታይ እንዲሆን የማያስገድዱ ወይም ገንዘብ ማግኘትን መሰረት ያደረገ ቃል መግባትን የሚያስወግዱ መሆን የሚሉት መስፈርቶች በግልጽ ሊደነገጉ ከሚገቡ ጉዳዮች መካከል ናቸው።

(10) ፈቃድ ለማግኘት "የድጋፍ ደብዳቤ" እንደሚያስፈልግ በረቂቁ ላይ በተደጋጋሚ ተጠቅሷል፡፡ ነገርግን የሃይማኖት ብሮድካስት ለማቋቋም ፈቃድ ከተሰጠ ተጨማሪ የድጋፍ ደብዳቤ ለምን ያስፈልጋል?

(11) ህዝባዊ አስተያየት አላማው፤ ሥነሥርዓቱ፤ ተሳታፊዎቹ እና በምን ጉዳይ ላይ የሕዝብ አስተያየት እነደሚሰጥበት በግልጽ መጠቀስ ይኖርበታል (ምሳሌ፡ አንቀጽ 12፤ 13)። ይህ የሃይማኖት ብሮድካስት ስለሆነ አስተያየት እንዲሰጥ መጠየቅ ያለበት የማኅበረሰብ ክፍል ወይም ተቋምና አስተያየቱ የሚመዘንበት መንገድ መቀመጥ አለበት። አስተያየት ሁሉም ቢሰጥ ችግር ባይኖረውም፤ ካሃይማኖቱ ተከታዮች የሚሰጥን አስተያየት ከሌሎች አስተያየቶች ጋር በአንድነት መመዘን አግባብ አይሆንም።

(12) የብሮድካስት አዋጁ አንቀጽ 42 እኛ 43(3) መሰረት አንዴ የተሰጠ ፍቃድ ወይም የታደሰ የብሮድካስት ፈቃድ ለ 10 ዓመት የፀና ነው ይላል። የረቂቁ አንቀጽ 11(3) ግን የአዋጁን አንቀጽ 43(4) በግልጽ በሚቃረን ሁኔታ የታደሰ ፍቃድ ለአንድ ዓመት እንደሚያገለግል እና በየዓመቱ እንደሚታደስ መደንገጉ በአዋጁ የተቀመጠውን የጊዜ ገደብ በመመሪያ ዝቅ ለማድረግ መሞከር ስለሆነ አግባብ አይደለም፡፡

(13) የረቂቁ አንቀጽ 12(1) እድሳትን በተመለከተ ፈቃጅ /permissive/ ድንጋጌ ቢሆንም ነገር ግን ከአዋጁ ውጭ በመሆኑ የሕዝብ አስተያየት ፍቃድን ለማደስ አስፈላጊ አይደለም፡፡ የሕዝብ አስተያየት መቼ እንደሚያስፈልግ በብሮድካስት አዋጁ አንቀጽ 38 እና ተከታዮቹ እንዲሁም ለፍቃድ እድሳት ምን እንደሚያስፈልግ እና እንደመስፈርት እንደሚታይ በአንቀጽ 43 ላይ ተደንግጎ ይገኛል። ነገርግን የሕዝብ አስተያየት መጀመሪያ ፍቃድ ሲሰጥ እንጅ እድሳት ላይ ሰለማስፈለጉ አልተጠቀሰም። ስለሆነም አዋጁ በግልጽ ያለፈውን ጉዳይ መመሪያው እንደአዲስ ግዴታ አድርጎ ማቅረቡ አግባብነት የለውም።

(14) የረቂቁ አንቀጽ 17(2) ግልጽ አልሆነልኝም፡፡ ምናልባት በፈቃዱ ላይ ከተመለከተው የፕሮግራም “ቻናል” ሌላ ፕሮግራሙን ማሠራጨት ከፈለገ ለባለስልጣኑ ማሳወቅ በቂ መሆን አለበት። ይኸንንም በአንቀጽ 18 ስር ማካተት ይቻላል።

(15) የረቂቁ አንቀጽ 19(1) መጀመሪያ ግን እርማት የሚያስፈልገው ጉዳይ መሆኑን ባለፍቃዱ ካመነበት ብቻ ተፈጻሚ እንደሚሆን ማመላከት ይገባል። ምክንያቱም ባለፈቃዱ "የቀረበው አቤቱታ እርማት አያስፈልገውም" ብሎ ካመነ፤ ቅሬታውን ይዞ ወደ ባለስልጣኑ የመሄድ መብት ሊኖረው ይገባል።

---------------- //

ሰኔ 10፤ 2014 ዓ.ም.